የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

https://t.me/sirius_logistics

ቁጥር/ Ref.No. 4-0/0647/18
ቀን/Date ነሐ 08 2017

**በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**
**<u>ባያሉበት</u>**

**ጉዳዩ፦ <u>የሲኖትራክ ተሽከርካሪ ወደ አገር እንዳይገባ የተጣለ ህግድን አስመልክቶ መረጃ ስለመስጠት፤</u>**

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በቁጥር ትሉ-2.4/74 ቀን 01/12/2017 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሲኖትራክ ተሽርካሪዎች ጋር ተያይዞ ካለው የጥራት እና ቴክኒክ ጉድለት ምክንያት በሰው ህይወት ላይ በየጊዜው አደጋ እየደረሰ ያለ በመሆኑ እነዚህ የጥራት ጉድለቶች በሲኖትራክ ካምፓኒው ማስተካከያ እስከሚደረግ ድረስ ከ27/09/2017 ዓ.ም ጀምሮ የሲኖትራክ ምርት የሆኑ ተሽርካሪዎች በሙሉ ወደ አገር እንዳይገቡ ስለተከለከሉ ምንም ዓይነት የማስገቢያ ፍቃድ መስጠት ያቆሙ ቢሆንም የሚኒስቴር መ/ቤታቸውን ፊርማ እና ማህተም በማስመሰል የሲኖትራክ ማስገቢያ ፍቃድ ለማሰራት የሚሞክሩ ሰዎች ያሉ መሆናቸውን ባገኙት መረጃ ያረጋገጡ መሆኑን በመግለጽ፤ ከ27/09/2017 ዓ.ም ወዲህ በሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው የተሰጠ የሲኖትራክ ማስገቢያ ፍቃድ የሌለ በመሆኑ ምንም ዓይነት አገልግሎት እንዳያገኙ እንዲደረግ በማሳወቅ የዚህ ዓይነት ሙከራ ሲደረግ በኮሚሽናችን በኩል ክትትል ለሚኒስቴር መ/ቤታቸው ጥቆማ እንድንሰጥ ጠይቆናል።

ስለሆነም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሲኖትራክ ተሽከርካሪን አስመልክቶ ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት ጥብቅ ጥንቃቄ እንዲደረግ እያሳወቅን፤ ሚኒስትር መ/ቤቱ ያሳወቀበትን ደብዳቤ 1 ገጽ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

መንግሥቱ ተፈራ አያና
የጉምሩክ ኮሚሽነር
ም/ቤት ኃላፊ

**<u>ግልባጭ፦</u>**

- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት

  **<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>**፤



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
ፖ.ሳ.ቁ. 2559